# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ከቅብጥ[1] ቤተክርስቲያን ጥገኝነት ነጻ ለማውጣት የተደረገ ትግል፣ ከ፲፱፻፲፰-፲፱፻፵፩ ዓ.ም[2]

ውዱ ጣፈጠ*

## መግቢያ

በዘመናችን ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በዝተው ብንመለከትም፤ የዛሬ ሰማንያ ዓመት አንድም ኢትዮጵያዊ ጳጳስ አልተሾመም ነበር። በየጊዜው የተነሣው ከጥገኝነት የመላቀቅ ጥያቄም ምላሽ አላገኘም ነበር። አሁን በዘመናችን እየተፈጸመ ያለውን ስንመለከትና ቀደም ብሎ የተፈጸመውን ስናጤን መገረማችን አይቀርም። የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ከተሾሙ በኋላ በየሀገረ ስብከታቸው ሲዘዋወሩ እነርሱን ለመመልከትና በመስቀላቸው ለመባረክ ሕዝቡ አገር ነቅሎ ይወጣ ነበር። በመስቀላቸው ለመባረክ ያልበቃው የረገጡትን የመሬት አፈር ለመዝገን ሽሚያና ርብርብ ያደርግ ነበር።

ይህ ጽሑፍ በቅድሚያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ራሷን ለማስቻል ስለተካሄደው የሃይማኖት ብሔርተኝነት ትግል በአጭሩ ቅኝት ያደርጋል። ከዚያም ከአምስቱ ዓመት የጠላት ወረራ በኋላ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስና ከዚያም ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ለማሾም ስለተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ይዳስሳል።

## "የሃይማኖት ብሔርተኝነት"[3] እንቅስቃሴ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአራተኛው ክፍለ ዘመን ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ የግብጽ ቅብጥ ቤተክርስቲያን ብቸኛዋ ትልቅ ሀገረ ስብከት ሆና ኖራለች። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የበላይ አለቃ በእስክንድርያ ቅብጥ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ተባርኮ የሚሾም ሊቀ ጳጳስና የግብጽ ዜግነት ያለው ሰው ነበር። የግብጽ ሊቀ ጳጳስ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ዋና ሥራ ነገሥታቱን ቀብቶ ማንገስ፣ ታቦት መባረክ፣ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን መባረክና መሾም ነው። ከእነዚህ ሥራዎች ውጪ በቤተክርስተሪያኗ አስተዳደር ላይ ሥልጣን አልነበረውም። ከ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እጨጌው (ከደብረ ሊባኖስ ገዳም እየተመረጠ የሚመጣ) በቤተክርስቲያኗ አስተዳደር ላይ ሥልጣን ነበረው። ከማንኛውም በላይ የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ባለሥልጣን ንጉሡ ነበር። የግብጹ ሊቀ ጳጳስ ጽሕፈት ቤት ከንጉሣዊው ቤተ መንግሥት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ሲሆን፣ እጨጌው ዓቃቤ ሰዓቱና (ከደብረ ሐይቅ ገዳም እየተመረጠ የሚመጣው) ሊቀ ካህናቱ ቤተክርስቲያኗን በማስተዳደር በኩል ቤተ መንግሥቱን ይረዱ ነበር። ንጉሡ ጳጳሱን የማጋዝ (ወደ ግዞት መላክ)፣ በምትኩም ሌላ ጳጳስ እንዲሾም የመጠየቅ፣ የሃይማኖት ጉባኤ የመጥራትና ይህንኑ ጉባኤ በበላይነት የመምራትና ውሳኔ ላይ የመጨረሻ ቃል የመስጠት ሥልጣን ነበረው። ንጉሡ በየጊዜው በሚነሡት የቀኖና ልዩነቶች ላይ የመወሰን፣ የታላላቅ አድባራት አለቆችንና ገዳማት መምህራንን የመሾምና የመሻር ሥልጣን ነበረው። ሊቀ ጳጳሱ የነበረው ዋነኛ ሥልጣን ማውገዝ ሲሆን ይህ ውግዘት የሚነሣበት ልዩ ልዩ አጋጣሚም ነበር።[4]

---

*ዶ/ር ውዱ ጣፈጠ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ሊቀመንበር ናቸው።

[1] የኮፕት ቤተክርስቲያን የምትባለው ለአንድ ሺሕ ስድስት መቶ ዓመት ያህል፤ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ስታስተዳድር የነበረችው የግብፅ እስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ናት። ቅብጥ የሚለው ቃል፤ ምንጩ "Coptic" የሚባል የጥንት ግብጻውያን ቋንቋ ነው።

[2] ይህ ጽሑፍ ከዚህ ቀደም በማኅበረ ቅዱሳን ጥናትና ምርምር ማዕከል ጳጉሜ ፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም. በተካሄደው ዓመታዊ ዐውደ ጥናት ላይ ለውይይት የቀረበ ነበር።

[3] በዚህ ጽሑፍ የሃይማኖት ብሔርተኝነት የሚለው አገላለጽ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕደ ቤተክርስቲያን ከግብጽ ቤተክርስቲያን ጥገኝነት ተላቃ ራሷን እንድትችልና ከራሷ የቤተክርስቲያን መሪዎችን/ጳጳሳትን/ እንድትሾም ሲደረግ የነበረውን የረጅም ጊዜ ትግል ይወክላል።

[4] Staurt Munro-Hay, *Ethiopia and Alexandria: The Metropolitan Episcopacy of Ethiopia* (Warszawa and Wiesbaden: Bibliotheca Nubia et Aethiopica, 1997), p. 174.

የግብጽ ጳጳሳት የአገራቱን ቋንቋ ስለማይናገሩ፣ ባሕሏንና ልማዷን ስለማያውቁ ከሕዝቡ የተገለሉ የሃይማኖት አባቶች ነበሩ፤ ስብከት ማካሄድና የሕዝቡን የሃይማኖት ፍላጎት ለመረዳት ስለማይችሉ። የግል ወይም ይፋ የሆነ ንግግር የሚያካሂዱት በአስተርጓሚዎች ርዳታ ነበር። አስተርጓሚዎቹ ዐረብኛ የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ወይም የአገራቱን ቋንቋ የለመዱ ቅብጦች ነበሩ። የግብጽ ጳጳሳት ከሕዝቡና ከኢትዮጵያውያን ካህናት ጋር የነበራቸው ግንኙነት እጅግ የተገደበ ከመሆኑም በላይ ወሳኝ የሆነ መንፈሳዊ አመራር ለመስጠት ይቸገሩ ነበር። አንዳንድ ጊዜም ጠለቅ ያለ የሃይማኖት ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ጳጳሳት ሆነው ይመጡ ነበር። አሳሳች ጳጳሳትም አንዳንድ ጊዜ ይመጡና ማንነታቸው እስኪጋለጥ ድረስ ሥልጣን ይይዙ ነበር። በአገራቱ የሃይማኖት ትምህርት መስፋፋት፣ የሥነ ጽሑፍ መዳበር፣የሥዕልና ሌሎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስደናቂና አኩሪ የሥራ ውጤቶች የተገኙት በኢትዮጵያውያን ካህናት ነበር።[5]

ግብጻውያን ጳጳሳትን ወደ አገር ለማስመጣት ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ለግብጹ ሡልጣንና ለቅብጡ ፓትርያርክ እጅግ ውድ የሆነ ስጦታ ይልኩ ነበር። እነዚህን ስጦታዎችም መክፈል ለአገራቱ መንግሥት ከባድ ነበር። የቅብጥ ጳጳሳት በኢትዮጵያ ውስጥ የተደላደለ ኑሮ ከመኖራቸውም በላይ የተመደበላቸውን ጉልት እንደ አንድ ዓለማዊ ገዢ ያስተዳድሩ ነበር። ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ይቀበሉ፣ በስራቸው ብዙ ገባሮችን ያስተዳድሩ፣ እንዲሁም ታቦት ለመባረክ፣ ለዲያቆናትና ለቀሳውስት ሥልጣነ ክህነት ለመስጠት ስጦታ ይቀበሉ ነበር።

አገራዊ ሊቀ ጳጳስን ወይም ፓትርያርክን ለማውጣት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ነጻ ለማድረግና ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጥገኝነት ለመላቀቅ የተካሄደው የሃይማኖት ብሔርተኝነት ስሜት በ፳ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያቹ ዐሥራዎች በድንገት የተጀመረ አልነበረም። ባለፉት ክፍለ ዘመናት ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ካህናት ሐሳቡን ሲያውጠነጥኑት ኑረዋል። ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ የማውጣት ዕቅድ በቅድሚያ በዛጉዌ ስርወ መንግሥት ጊዜ በንጉሥ ሀርቤ ዘመነ መንግሥት ተወጥኖ ነበር። በንጉሥ ላሊበላ ዘመን ኢትዮጵያውያን ኤጲስቆጶሳት ተሹመው እንደነበር የሚገልጽ ታሪካዊ መረጃም አለ። በንጉሥ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የመንፈሳዊ ነጻነት ስሜት እያደገ መጥቶ ካህናቱ በንጉሡ ዙርያ በመሰባሰብ የብሔርተኝነት ስሜት ጠንካራ መግለጫ እስከመሆን ደርሶ ነበር። በልጁና በሥልጣን ወራሹ በንጉሥ በዕደማርያም ዘመነ መንግሥት ሰባት መቶ ኢትዮጵያውያን ካህናት የተሰበሰቡበት ታላቅ የሃይማኖት ጉባኤ ተካሂዷል። የአብዛኛው ተሰብሳቢ ፍላጎት (አራት መቶ የሚሆኑት) ነጻነትን ለማወጅና ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነትና ጥገኝነት ለማቋረጥ ያለመ ነበር። ነገር ግን ይህንን የሃይማኖታዊ ብሔርተኝነት ዓላማ ንጉሡ ስላልደገፈው ሳይሳካ ቀረ። ይሁን እንጂ የሃይማኖታዊ ብሔርተኝነቱ ስሜት በአገራቱ ውስጥ የጎላና የጠነከረ ተቀባይነት እንዳለው ያስመሰከረና ለቅብጥ ቤተክርስቲያን ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ያስተላለፈ ነበር፡[6]

ከአራት ክፍለ ዘመናት በኋላ እስከ ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ፬ኛ ዘመን ድረስ የሊቀ ጳጳሳቱ ሀገረ ስብከት መስፋፋት ጉዳይ አልተነሳም ነበር።

---

[5] Otto F. Meindarus, *Christian Egypt, Faith and Life* (Cairo: Cairo American University Press, 1970), p. 390; ኀሩይ ወልደሥላሴ፣ *ዋዜማ* (አዲስ አበባ፤ጎነ ጽባህ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፷፩፻፣ ገጽ ፺፵-፺፷።

[6] Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527* (Oxford: Clarendon Press, 1972), pp. 245-7; Gerard Colin, “Le Synaxaire Ethiopien, Mois de Miyazya” *Patrologia Orientalis*, t -46, 4 No. 208, Brepolis-Tornhaoul / Belgique, 1995, pp. 526-7; E.A. Wallis Budge, trans. and ed. *The Books of the Saints of the Ethiopian Church* (Cambridge: 1928), pp. 185-6; II, pp. 800-01

በአገሪቱ ላይ የሚሾመው በአብዛኛው ጊዜ አንድ የቅብጥ ጳጳስ በመሆኑ እርሱ መላ አገሪቱን በሥራ ለማዳረስ አይችልም ነበር።[7] ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ አራት የቅብጥ ጳጳሳትን አመጡ። እነዚህን ጳጳሳት በተለያዩ ግዛቶች (ትግራይ፣ሸዋ፣ጐጃምና ወሎ) በመመደብ የጳጳሳት ሀገረ ስብከት እንዲፈጠር አደረጉ። ከእነዚህ አራት ጳጳሳት መካከል በሸዋ ውስጥ እንዲቀመጡ ለንጉሥ ምኒልክ ተሰጥተው በነበሩት በአቡነ ማቴዎስ ዘመን የአገሪቱን ቤተክርስቲያን ነጻ ለማድረግ የሃይማኖት ብሔርተኝነት እንደገና ተቀሰቀሰ።

የግብጽ ቅብጥ ቤተክርስቲያንን የበላይነት የሚቃወም ሕዝባዊ ጩኸት የተቀሰቀሰው *ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ታትሞ* በወጣው *ብርሃንና ሰላም* ሳምንታዊ ጋዜጣ እጅግ አስደንጋጭና አሰዛኝ ዜና ነበር። ጋዜጣው የዓባይ ወንዝ ጎርፍ ስለ ወሰዳቸው አርባ ልጆች ዘገባ አቅርቦ ነበር። በጎርፍ የተወሰዱት ልጆች የዲቁና ሹመት ለመቀበል ወደ ጳጳሱ መኖርያ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዙ ወጣቶች ነበሩ። በሚያዝያ ወር ፲፱፻፲፰ ዓ.ም የተመዘገበው የሞት አደጋ ብቻ በድምሩ ሰማንያ አምስት ነበር።[8]

ሌሎች ዘጋቢዎች ደግሞ ዲቁናና ቅስና ለመስጠት እንዲሁም ታቦት ለመባረክ ጳጳሱ ገንዘብ እንደሚቀበሉ ይህም ከሩቅ አገር ተጉዘው ለሚመጡ ሕፃናትና ቀሳውስት ችግር የፈጠረባቸው መሆኑን አስረድተዋል። በጊዜው የነበሩት ጳጳስ ጨካኝ፣ ገንዘብ ሰብሳቢና ለልጆች መሰቃየት ደንታ የሌላቸው መሆኑን የሚያመለክት ጠንካራ ተቃውሞ ነበር። ለክህነት የሚከፈለው ገንዘብ ጉዳይ በ፳ኛው ክፍለ ዘመን ብቻ የተነሣ ሳይሆን ቀደም ብሎም በተደጋጋሚ የተነሣ ጉዳይ ነበር። በ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን በገዳም መነኮሳት የሚመራ የለውጥ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። በጊዜው በደቡብ የአማራ ክልል የደብረ ጎል ገዳም መምህር በጸሎተ ሚካኤል የቅብጡን ጳጳስ አቡነ ዮሐንስን ክህነት ለመስጠት ገንዘብ ተቀብልሀል ብሎ በንጉሥ ዓምደጽዮን ዙፋን ችሎት ከሶት ነበር። ነገር ግን ክሱ በንጉሡ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።[9]

ከሁሉም ይበልጥ በዚህ ዘመን የተነሡትን የሃይማኖት ብሔርተኞች ያሳሰባቸው ኢትዮጵያውያን ለምን የጳጳስነት ሹመትና ማዕረግ እንደተከለከሉ ነበር። ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓ.ም የወጣው የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መጣጥፍ በኢትዮጵያ የቅብጡን ጳጳስ ሥልጣን የሚወስነውን *የፍትሐ ነገሥቱን* ቀኖናዊነት በመቃወም ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመ ጽሑፍ ነበር።

*ፍትሐ ነገሥት* ግብጾች በሀሰት የጨመሩትን ስርዋጽ ሕግ የያዘ ኢትዮጵያውያንን የሊቀ ጳጳሱን መንበር ከመያዝ የሚከለክውን በ፫፻፲፯ ዓ.ም በኒቂያ ጉባኤ የተካሄደውን ውሳኔ የያዘ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በንጉሠ ነገሥት ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ሲሆን፣ በሃይማኖት በኩል ተቀባይነት ያለው ሕጋዊና ቤተክህነታዊ ክርክሮችን ለመፍታት የሚረዳ ነው።[10]

---

7 H.M. Haytt, The Church of Abyssiania (London: Luzac & Co., 1928), p. 46; መርስኤ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ* (አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፵፮)፣ ገጽ፲፮።

8 ብርሃንና ሰላም፣ *ቁ ፲፮፣ ሚያዝያ ፲፩፣ ፲፱፻፲፰፣ ገጽ ፲፱፻፳፯÷ ቁ. ፲፱፣ ግንቦት ፫፣ ፲፱፻፲፰፣ ገጽ ፳፮።*

9 *ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. ፳፩፣ ሰኔ ፲፣ ፲፱፻፲፰፣ ገጽ ፩፻፺፩።*

10 Adugna Amanu, “The Ethiopian Orthodox Church Becomes Autocepahlus,” BA Thesis, Haile Selassie I University, June 1969, p. 13.

ከላይ የተጠቀሰው ሕግ በመጽሐፉ አንቀጽ ፴፪ የሚገኝ ሀሰተኛ አንቀጽ ነው። እርሱም ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ሰው መካከል ጳጳሳትን እንዳይመርጡና በኢትዮጵያ የሚቀመጠው የግብጽ ጳጳስም በሥሩ ሌሎች ጳጳሳትን ቀብቶ እንዳይሾም ይከለክላል። ይህ ጉዳይ ቀደም ብሎም ንጉሥ ዘርዓያዕቆብንና ቤተክርስቲያኗን ያሳሰበ ነበር። ዘርዓ-ያዕቆብ ኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት በለገሳቸው የሲኖዶስ መጽሐፍ ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሊቀ ጳጳስ ሊሾሙ እንደሚችሉ የሚገልጽ አንቀጽ አለው።[11] ይሁን እንጂ እስከ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ዓመታት ድረስ ኢትዮጵያውያን ለዚህ ሹመት አልበቁም ነበር።

የጊዜው ጸሐፊዎች (የሃይማኖት እንቅስቃሴ ከተጀመረበት ከ፲፱፻፲፰ ዓ.ም. ጀምሮ) የቅብጡ ጳጳስ ኢትዮጵያውያንን እንዲሾሙ ጥያቄ አቀረቡ። አንድ ግብጻዊ ጳጳስ የአገሪቱን መንፈሳዊ ፍላጎት ማርካት ስለማይችል፣ ሃይማኖትንም ለማስፋፋት ብዛት ያላቸው ጳጳሳት መኖር የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ማስከበር መሆኑን በመግለጽ ተከራከሩ። ግብጻውያን ጳጳሳት የሃይማኖት ትምህርት ቤት አለመክፈታቸውን፣ ከሀገሪቱ የሚሰበስቡትን ገንዘብ ወደ አገራቸው እንደሚያሻግሩና፣ ክህነት ለማግኘት ልጆች ገንዘብ መክፈላቸውን በመቃወም ጻፉ።[12]

ከሚያዝያ እስከ ነሐሴ ፲፱፻፲፰ ዓ.ም የታተሙት ጽሑፎች የብሔርተኝነትን ሐሳብ የሚያቀነቅኑ ነበሩ። ጥያቄአቸው ሌሎች ጳጳሳትን መቀባት የሚችል ነጻ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ እንዲኖር ነበር። የግብጽን የበላይነት አጥብቀው ይቃወማሉ። ለውጥ ደጋፊዎችና ብሔራዊ መብትን የሚደግፉ ሰዎች በስፋትና በጥልቀት በጉዳዩ ላይ ተከራከሩ። ወግ አጥባቂዎችና የጳጳሱ ደጋፊዎች የሆኑ ሰዎች በጉዳዩ ዙርያ መጻፍ የጀመሩት አሰቃቂው አደጋ ከደረሰ ከአራት ወራት በኋላ ነበር። በዚህ ምክንያት ስለ ወግ አጥባቂነት ሐሳብ ደጋፊዎች ጥንካሬ ብዙ ነገር አናውቅም። እነዚህ ወግ አጥባቂዎች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር የነበራት ታሪካዊ ትስስር እንዲቋረጥ የሚፈልጉ አልነበሩም። ክህነት ለማግኘትና ታቦት ለማስባረክ ገንዘብ መክፈል ቀደም ያለና የተለመደ አሠራር በመሆኑ ጳጳሱ ያደረገው አዲስ ነገር የለም በማለት የመቃወሚያ ሐሳብ ያቀርባሉ።[13]

በዚህ የሃይማኖት ብሔርኝነት ክርክር ሂደት ወቅትም ንጉሣዊው ቤተመንግሥት በበኩሉ ቤተክርስቲያኗን በሚመለከት አዲስ ሕግ ለማውጣት ተገደደ። የለውጥ ፈላጊ ተራማጆች ጥንታዊውን ልማድ ከመሠረቱ በመነቅነቅ ሕዝቡን የኒቂያ ጉባኤ *ፍትሐ ነገሥት* ውስጥ እንደተጻፈው የኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ሹመትን በሚመለከት ያለበትን ስህተት ለሕዝቡ አሳወቁ። ሐሳባቸው በሕዝቡ ዘንድ ሲሰርጽ ሕዝባዊ ግፊት እየጨመረ መጣ። ቤተመንግሥቱም የጳጳሱን ሥልጣን ለመገደብ ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ ወደ መስጠት አዘነበለ። ንግሥት ዘውዲቱና ራስ ተፈሪ በመስከረም ፬/፲፱፻፲፱ ዓ.ም በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ሕግ ለቤተክርስቲያኒቱ ደነገጉ። ሕጉ ፳፰ አንቀጾች አሉት።

[11] Vat. Borg. Etiop, 2, 1326, Catalogued by Silvanus Grebaut et Eugenius Tisserant, Codices Aethiopci Vaticani et Borgiani Barberinins Orientalis 2, Rossianus 865, Vol. I, Vatican City, 1935, pp. 767-782.

[12] ብርሃንና ሰላም፣ ቁ.፴፣ ሐምሌ ፳፪፣ ፲፱፻፲፰፣ ገጽ ፪፻፴፯።

[13] Gabre Egzi'abher Elyas, *Prowess, Piety and Politics: The Chronicle of Abeto Iyyassu and Empress Zawditu of Ethiopia, 1900-1930*. ed. and tarns. Reidulf K Moliver (Kon: Rodiger Koppe Verlag, 1994), P. 199; ብርሃንና ሰላም፣ ቁ፥፴፬፣ ነሐሴ ፳፮፣ ፲፱፻፳፮፣ ገጽ ፪፻፰፰-፪፻፰፱።

የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ አንቀጾች የቅዱስ ሲኖዶሱን ወይም የመንፈሳዊ ጉባኤውን መብትና ሥራ ይደነግጋል። የቤተክህነቱ ጽሕፈት ቤት መቋቋምን የሚያመለክቱም አሉ። ሦስት ያህል አንቀጾች ካህናትንና ታቦት ከመባረክ ሥራ በስተቀር ቤተክርስቲያኗን የማስተዳደር ሥራ የእጨጌው መሆኑን ይደነግጋል። እጨጌው የቤተክህነቱን ጽሕፈት ቤትና መንፈሳዊ ጉባኤ በበላይነት የመምራት መብት ተሰጠው። የጳጳሱ የበላይ ሓላፊነት በቤተክህነቱ የሚቀርቡላቸውን ቀሳውስትና ዲያቆናት መባረክ ብቻ እንደሆነ ይወስናል። የቀሳውስትንና የዲያቆናትን ክህነት አሰጣጥ የሚከታተልና ሌሎች አስፈላጊ ኮሚቴዎችንም አቋቋመ። በዚህ የሥራ ሂደት በጊዜው የነበሩት ጳጳስ ምንም የሥራ ድርሻ አልነበራቸውም።[14]

ፈር ቀዳጅ የሆነው ይህ የቤተክርስቲያኗ ደንብ መንፈሳዊ ጉባኤ ለመጀመሪያ ጊዜ በማቋቋሙ፣ የሃይማኖት ጉዳዮችን የእጨጌው ሓላፊነት በማድረጉ፣ የግብጹን ጳጳስ ሥልጣን በመገደቡና፣ የሃይማኖት ብሔርተኞች ጥያቄ በከፊልም ቢሆን በመመለሱ የሕጉ መውጣት አንድ እርምጃ ነበር። የመንፈሳዊ ጉባኤው ሥራ የክህነት ሥራን ብቻ እንዲመለከት ሲደረግ ዓለማዊ የሆኑ ነገሮችን እንዲመለከት አይፈቅድለትም ነበር።
የሃይማኖት ብሔርተኞች ስፋት ያላቸውን ጉዳዮች በማንሳት በጥልቀት መከራከርና መጠየቅ ጀመሩ። እነዚህም የግብጽ የበላይነትና ጥገኝነት፣ "የግብጽ ቀንበር"፣ "ከባድ ሸክም"፣ 'የዜጋ/ ዜግነት/ ገባር/ ገባርነት ግንኙነትና'፣ "ባርነትና የሃይማኖት ባርነት" የሚሉ ነበሩ። የቀለም ልዩነት- ጥቁርና ነጭ- እንዲሁም የዘር መድልኦ የሚሉ ጉዳዮች ተነስተው ነበር። ብሔርተኞቹም ነጻ ቤተክርስቲያን ለነጻ መንግሥት እያሉ ተከራከሩ። ግብጻውያን በኢየሩሳሌም ያለውን የኢትዮጵያ የዴር ሡልጣን ገዳምን ለመውሰድ የሚያደርጉትን ጥረት ተቃወሙ።

የብሔርተኞቹ ዋና ግብ የግብጻውያንን የበላይነት ባለመቀበል ላይ ያተኮረ ነበር። በእስክንድርያና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አይደለም በማለት ይህንኑ ያስረግጣሉ። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በእስክንድርያ ቅብጥ ቤተክርስቲያን የተጨቆነ ነው ይላሉ። ግንኙነታቸው በጌታና በገባር ላይ የተመሠረተ ነው በማለት ይከራከራሉ። ይህንን ለመግለጽ የተጠቀሙባቸው ቃላት ዜጋ/ዜግነት ወይም ገባር ናቸው። ጳጳስ ለማስመጣት ይከፈል የነበረው ስጦታ የኢትዮጵያን መንበረ ጵጵስና በሞኖፖል ለያዙት የግብጽ ጌቶች የሚከፈል ግብር ነው በማለት ይቃወማሉ። የሁለቱን አብያተክርስቲያን ግንኙነትም ከቅኝ ግዛት ጭቆና ጋር ያነጻጽሩት ነበር። አንዳንዶቹ ግንኙነቱን በባሪያና በጌታ መካከል ካለ ግንኙነት ጋር ያመሳስሉታል። የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የባሪያ ጌታ ስትሆን የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት በባርነት ስር ያለች ያደርጓታል። አንዳንዶቹ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ የተጫነ የሃይማኖት ባርነት ነው በማለት ምሬታቸውን ይገልጻሉ። የባሪያ ጌታ በፈቃዱ ለባሪያው ነጻነት ስለማይሰጥ ነጻነታቸውን ለማወጅ ሁሉም እንዲረባረብ ይጠይቃሉ።[15]

ነጻይቱ ኢትዮጵያ የራሷ ሀገራዊ የጵጵስና አመራር ሳይኖራት በቅኝ ግዛት ስር ያሉት ሶርያና አርመን የራሳቸው የሆነ ነጻና ብሔራዊ አብያተክርስቲያን አላቸው በማለት ተቆጩ። ሁኔታውንም ይህን በመሰለ አእምሮን በሚነካ ግጥም ይገልጹት ነበር። የሚከተለውን ግጥም የገጠሙት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ነበሩ።

[14] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፣"የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ደንብ" መስከረም ፫፣ ፲፱፻፲፱ EMML ቁ. ፲፩፻፵፩።
[15] ብርሃንና ሰላም፣ ቁ. ፮፣ የካቲት ፫፣ ፲፱፻፲፱፣ ገጽ ፵፪፣ ቁ. ፲፩፣ መጋቢት ፳፣ ፲፱፻፲፱፣ ገጽ ፹፩፤ ቁ. ፲፯፣ ሚያዝያ ፮፣ ፲፱፻፲፱፣ ገጽ ፩፻፲፫ እና ቁ. ፲፰፣ ሚያዝያ ፳፯፣ ፲፱፻፲፱፣ ቁ. ፩፻፵።

*ንጉሥ ሳይኖራቸው ሶርያና አርመን*
*መርጠው ይሾማሉ ባትርያርክና አቡን*
*ከወገኑ መርጦ ጳጳስ የማይሾም*
*ከጦብያችን በቀር ሌላ ሕዝብ የለም።*[16]

ስለ ሁለቱ አብያተክርስቲያን ግንኙነት ሲካሄድ የነበረው የተጧጧፈው ውይይት የብዙ ነገሮች ውጤት ነበር።ዘመናዊ ትምህርት ዘመናዊ አስተሳሰብን አመጣ። ይህ ክፍለ ዘመን ስለአገሪቱ ኋላቀርነትና ስለለውጥ አስፈላጊነት ውይይት የተጀመረበት ጊዜ ነበር። ትምህርት የምዕራባውያንን የቴክኖሎጂ እድገት ብሎም ዘመናዊነትን በሀገሪቱ ለመትከል ትልቅ ቁልፍ መሆኑን የዘመኑ ምሁራን ተገንዝበው ነበር። ኢትዮጵያውያን መሪዎች የትምህርት መስፋፋትን እንዲያፋጥኑና አስተዳደራቸውን ዘመናዊ እንዲያደርጉ ይጠይቁ ነበር። ወደ ውጭ አገር የተላኩ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ኋላቀርነት እየተገነዘቡ ወደ አገራቸው ተመለሱ። የሥልጣኔና የዕድገት ዋና ምሳሌያቸውም ጃፓን ነበረች። በጋዜጣ ኅትመት መጀመር አስፈላጊ የሆነውን የውይይትና የዘመናዊ ሐሳብ መለዋወጫ መድረክ ፈጠሩ። በተለይ ደግሞ አገሪቱ ላይ ስለሰፈነው የውጭ ተጽዕኖ፣ የጎረቤት የቅኝ ገዢ ኃይሎች ኢትዮጵያ ወደ ባሕር መውጫ በር ያላትን መብት ማሳጣታቸውና የጦር መሣሪያ እንዳታስገባ መከልከላቸው ያንገበግባቸው ነበር።ይህ ቁጭት የቅብጥ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ያላትን የበላይነት በሚቃወመው የሃይማኖት ብሔርተኝነት ትግል ውስጥ በጉልህ ተንጸባርቆ ነበር። የጸረ ግብጽ ተቃውሞ እያየለ ከመሄዱም በላይ የዚህ ተቃውሞ ቀንደኛ መሪዎች የወቅቱ ምሁራን ነበሩ።[17]በተጨማሪም በነጻ የምትኖር አገር ነጻ ቤተክርስቲያን ሊኖራት ይገባል በማለት ጥያቄአቸውን አጠናከሩ።[18] በአጠቃላይ ሲታይ በጊዜው የተስተጋባው መሠረታዊ ጥያቄ ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነጻነትና የቤተክህነቱን የሥልጣን ተዋረድ ኢትዮጵያዊ ማድረግ ነበሩ።

ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ የግብጹን ሊቀጳጳስ እንዲያግዙ እጨጌውን ጳጳስ አድርገው ለመቀባት ተስማሙ። ይሁን እንጂ ፓትርያርኩ በሐምሌ ወር ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ስላረፉ ለሚቀጥሉት ፲፯ ወራት ጉዳዩ ምንም እልባት ሳያገኝ ቀረ። ከዚያም በግንቦት ፳፫/፲፱፻፳፩ ዓ.ም. አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ካይሮ ላይ ተቀቡ። እነርሱም አቡነ አብርሐም፣ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤልና አቡነ ይስሐቅ ነበሩ። የቅብጥ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስም ከእነርሱ ጋር በአንድ ላይ ተቀቡ።[19] የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት መሾም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ትልቅ ስፍራ አለው። የመጀመሪያ የሆነውን ብሔራዊ የሥልጣን ተዋረድ የሚያዋቅርና የመጀመሪያውን የሀገረ ስብከት አደረጃጀት የሚዘረጋ ትልቅ እርምጃ ነበር። ይህንን አስመልክቶ አባ ተስፋ ሚካኤል የተባሉ ካህን ታሪካዊ ድርጊቱን በሚቀጥለው ቅኔ በአጭሩ ቋጨት።

ኃይለ ሥላሴ ንጉሥነ በጽሐ
ዮም ለኢትዮጵያ ንዜኑ ፍስሐ
ለዘመነ መንግሥትከ ጴጥሮስ ወአብርሐም
ይስሐቅ ወሚካኤል ኮንዋ አርአያሃ
ዮም ንዜኑ ፍስሐ
እስመኮነ ብርሃን ወጸብሐ።[20]

[16] ደስታ ተክለወልድ፣ *ገበታ ሃዋርያ የንባብ መማሪያ* (ድሬዳዋ፣ ቅዱስ አልአዛር ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፳፰)፣ ገጽ ፵-፵፩)።

[17]Wudu Tafete, "The Ethiopian Orthodox Church: The Ethiopian State and Alexandrian See, Indigenizing the Episcopacy and Forging National Identity, 1926-1991," Ph. D. Dissertation, University of Illinois at Urbana –Champaign, 2006, pp. 57-62 Bahru Zewde, *Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of Early Twentieth Century* (Oxford: James Currey,2002), pp. 24, 68-69, 99-137.

[18] ብርሃንና ሰላም፣ ቁ. ፮፣ የካቲት ፫ ፲፱፻፲፱፣ ገጽ ፵፩-፵፫።

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. ፳፬፣ ሰኔ ፮፣ ፲፱፻፳፩፣ ገጽ ፩፻፺፰።

[20] ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. ፳፮፣ ሰኔ ፳፣ ፲፱፻፳፣ ገጽ ፳።

ኃይለ ሥላሴ ንጉሳችን ደረሰ
ዛሬ ለኢትዮጵያ የምስራቹን እናብስር
ጴጥሮስ አብርሐም ይስሐቅና ሚካኤል የዘመንህ አርአያ ሆነዋልና
ዛሬ ለኢትዮጵያ የምስራቹን እናብስር
ብርሃን ስለሆነ ቀኑም ስለነጋ፡፡

ከስድስት ወራት በኋላ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጡ፡፡ በራስ ተፈሪ ጥያቄ በጥር ፩/፲፱፻፳፪ ዓ.ም እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቡነ ሳዊሮስ ተብለው በበዓታ ቤተክርስቲያን ተቀቡ፡፡[21]ይህም የኢትዮጵያውያን ጳጳሳትን ቁጥር ወደ አምስት አደረሰው፡፡ አቡነ ሳዊሮስ የእጨጌውን ማዕረግ ከጳጳስነታቸው ጋር ደርበው በመያዛቸው ከእርሳቸው በኋላ የመጡት ፓትርያርኮችም ማዕረጉን ጨምረው እንዲይዙት ተደረገ፡፡

በየካቲት ፲፱፻፳፫ ዓ.ም የጳጳሳቱ መተዳደሪያ ጉዳይ ውሳኔ ተሰጠው፡፡ የወር ቀለብ (ደመወዝ) ተመደበላቸው፡፡ መሬትም ተሰጣቸው፡፡ አገሪቱም በአምስት ታላላቅ አህጉረ ስብከቶች ተከፍላ በቤተመንግሥቱ የሥራ መመሪያ እየተሰጣቸው ተመደቡ፡[22]

## በጣልያን ወረራ ወቅት

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ጣልያን ኢትዮጵያን እንደወረረች ጳጳሳቱ ከመንግሥትና ከአርበኞች ጋር በመሆን ወራሪውን ጠላት ተከላከሉ፡፡ ከአምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት መካከል አቡነ ሳዊሮስ (የእጨጌውን ሥልጣን እንደያዙ ነበሩ) ቀደም ብሎ አርፈው ነበር፡፡ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ማይጨው ከመዝመታቸውም በላይ ከደጃዝማች አበራ፣ ደጃዝማች አስፋወሰን ካሳና ከሌሎችም ጋር በመሆን አዲስ አበባን ነጻ ለማድረግ በተካሄደው ሙከራ ወቅት ተያዙ፡፡ የጣልያንን ቅኝ አገዛዝ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምክንያት በሐምሌ ፳፪/፲፱፻፳፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ፡፡ የኢሉባቡር ጳጳስ አቡነ ሚካኤልም በትግሉ ውስጥ ሲሳተፉ ተይዘው የጥቁር አንበሳ አርበኞች ማኅበርን በመደገፋቸው በኅዳር ፳፬/፲፱፻፳፱ ዓ.ም እንደ አቡነ ጴጥሮስ በጥይት ተደብድበው ተገደሉ፡፡ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ለአገራቸው ነጻነት መስዋዕትነትን ከፍለዋል፡፡ አቡነ ይስሐቅ በጣሊያን ተይዘው በናኩራ ደሴት ከዚያም ወደጣልያን ተወስደው ከታሰሩ በኋላ ተለቀው ወደአገራቸው ተመለሱ፡፡ ከዚያም እጨጌ ሆነው በጣልያን አስተዳደር ተሹመው አገልግለዋል፡፡ የጎንደርና የጎጃም ጳጳስ የነበሩት አቡነ አብርሐም እጃቸውን ለጣልያን ሰጥተው የጣልያንን መንግሥት አገልግለዋል፡፡[23]

የጣልያን የቅኝ ግዛት አስተዳደር በኅዳር ወር ፲፱፻፳፱ ዓ.ም የሃይማኖት ጉባኤ ጠርቶ አቡነ አብርሃምን ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ አስመረጣቸው፡፡ በዚህ ጊዜ የቅብጥ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ አገራቸው ተመልሰው ነበር፡፡ የጣልያን መንግሥት ቤተክርስቲያኗን ከእናት ቤተክርስቲያኗ በመገንጠል እራሷን እንድትችል አደረገ፡፡ ይህም በእንግሊዝ መንግሥት ሥር ከነበረችው ግብጽ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይደረግ በማሰብ ነበር፡፡

[21] ዝኒ ከማሁ፣ ቁ. ፫፣ ጥር ፰፣ ፲፱፻፳፪፣ ገጽ ፲፯-፳፪፡፡
[22] ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል፣ *ዝክረ ነገር* (አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፶፱)፣ ገጽ ፫፻፴፯-፫፻፵፩፡፡
[23] Wudu, pp. 81-92.

ለቤተክርስቲያኗ አዲስ ሕግ በመስጠት፣ ቤተክርስቲያኗ በዐስር አህጉረ ስብከት እንድትደራጅ ተደረገ። ለዚህም ሲባል አቡነ አብርሃም ስድስት ጳጳሳትን ቀብተው ሾሙ። ይሁን እንጂ ያለእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ዕውቅና አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ ሆነው በመሾማቸው፣ እርሳቸውም ሌሎች ጳጳሳትን በመሾማቸው እንዲሁም ቤተክርስቲያኗ ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን በመለየቷ የተበሳጨው የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ድርጊቱን በጥብቅ አወገዘ።[24]

አቡነ አብርሃም በሐምሌ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ስላረፉ ሌላ ምርጫ ማካሄድ አስፈለገ። በመስከረም ፲፱፻፴፪ ዓ.ም በተካሄደው መንፈሳዊ ጉባኤ አቡነ ዮሐንስ በጣልያን ቅኝ አገዛዝ ስር ሁለተኛው ሊቀ ጳጳስ ሆነው ተመረጡ። እርሳቸውም ሌሎች ስድስት ጳጳሳትን ሾሙ።[25] ይህም በጣልያን ቅኝ አገዛዝ ስር ብዙ ጳጳሳትና በርከት ያሉ አህጉረ ስብከቶች መሾማቸውንና መከፈታቸውን ያጤኗል። ምንም እንኳን የቅኝ ገዢ ሥራና ውጤት ቢሆንም ቤተክርስቲያኗ ከእስክንድርያ ተለይታ ራሷን እንድትችል መደረጉን ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ካህናት ይፈልጉት እንደነበር ያስታውሷል። የኢትዮጵያ ነጻነት እንደተመለሰም በኢትዮጵያና በእስክንድርያ አብያተክርስቲያን መካከል በተደረገው ድርድር የኢትዮጵያ ካህናት የክርክራቸው መነሻ ያደረጉት የጣልያን ቅኝ ግዛት መንግሥት ያደረገውን ነበር።

## በኢትዮጵያና በቅብጥ መካከል የተደረገው የክርክር አጣብቂኝ

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማቸው ከመመለሳቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን አመራር ይዘው የነበሩት በጣልያን የተሾሙት ሁለተኛው ሊቀ ጳጳስና ሌሎች ጳጳሳት ለንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ጻፉ። በጣልያን ጊዜ ቤተክርስቲያኗ በሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ስር እንዳትገባ ሲሉ በጠላት ስር ሆነው ያስተዳደሯትን ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ንጉሡን ጠየቁ። ይሁን እንጂ በጠላት የተሾሙና የተዳደሩ እንዲሁም የጣልያን ተባባሪ መሆናቸውን በመገንዘብ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ እንደገቡ ሁሉም ጳጳሳት በቤት ውስጥ ቁም እስር እንዲቀመጡ ተደረገ። የቤተክርስቲያኗንም አስተዳደር ሥራ በስደት ኢየሩሳሌም የነበሩት እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እንዲረከቡ ተደረገ። እንዲሁም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ በቅብጥ ቤተክርስቲያን የተጣለው ውግዘት እንዲነሳ ለማድረግ ዝግጅት ተጀመረ።[26]

የቅብጥ ቤተክርስቲያንም በበኩሏ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የነበራትን መብት እንደገና ለመጨበጥ ስትል ለድርድር ተዘጋጅታ መልዕክተኞቿን ላከች። ከዚህ ቀደም ብሎ በሐምሌ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ትልቅ መንፈሳዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሂዶ ነበር። የተሰበሰቡትም ሰባ ሁለት የቤተክርስቲያኗ ሊቃውንት ነበሩ። አብዛኛዎቹ ተሰብሳቢዎች ቤተክርስቲያኗ ነጻ እንድትሆን ጠየቁ። እነዚህ የሃይማኖት ብሔርተኝነት ጠንካራ ደጋፊዎች ነበሩ። ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር ምንም ዓይነት ድርድር እንዲካሄድ አይፈልጉም። የክርክራቸው መሠረትም በጣልያን ጊዜ ነጻ የነበረችውን ቤተክርስቲያን አቋም የተመረኮዘ ነበር። የቅብጥ ቤተክርስቲያንን ውግዘትም አይቀበሉም። ሌሎቹ ቤክርስቲያናቸው ነጻ እንድትሆን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንን ፈቃድ ማግኘት ይገባል ባዮች ሲሆኑ፣ እስክንድርያ ይህንን ለመስጠት ካልፈቀደች ቤተክርስቲያናቸው ነጻነቷን እንድታውጅ ፈለጉ። አንዳንዶችም የቅብጥ ውግዘት ተፈጻሚነቱን የሚቀበሉና ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ሊሆን የማይችል የሚመስላቸውና ሃይማኖታዊ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ የማይፈልጉ ነበሩ።[27]

[24] የሮማ ብርሃን፣ ቁ.፩፣ ታኅሣሥ ፩፣ ፲፱፻፴፪፤ Matthew, “The Church of Ethiopia During the Italian Occupation,” October 27, 1943, p. 1 እና የኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ መዝገብ ቤት፣ ‹‹ፍርድ፣ የግብፃዊት ኦርቶዶክሳዊት የቅዱስ ጉባኤ በአባ አብርሃም እና በሀበሻ የጎጃም ጳጳስ የተደረገው ግዝት ነው።›› ታኅሣሥ ፲፣ ፲፱፻፳፱።
[25] የሮማ ብርሃን፣ ቁ. ፬፣ መስከረም ፲፯፣ ፲፱፻፴፪
[26] መንበረ ፓትርያርክ መዝገብ ቤት፣ ማቀፊያ ቁጥር 3384፣ ባህል ሚኒስቴር ብሔራዊ ቤተመዛግብት፣ መርስኤኃዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ፋይል ቁጥር 05-02፣ ገጽ ፴፩-፴፪።
[27] የሲኖዶስ ፋይሎች፣ ሐምሌ ፱፣ ፲፱፻፴፫።

የቅብጥ ቤተክርስቲያን ውግዘቱን ለማንሳት ፈቃደኛነት ብታሳይም እንደ አዲስ የተቀሰቀሰው ሃይማኖታዊ ብሔርተኝነት እጅግ ስጋት ላይ ጣላት። የርሷ ፍላጎት በጣልያን ጊዜ አገሪቱን ለቀው የሄዱትን የቅብጡን ጳጳስ አቡነ ቄርሎስን ወደ ሥልጣናቸው መመለስ ነበር። ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመቀባትም አሻፈረኝ አለች። ነገር ግን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ለመክፈትና አማርኛ ሊናገሩ የሚችሉ የቅብጥ ጳጳሳትን ለመሾም እንደምትፈልግ ገለጸች። መሠረታዊ የሆነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ነፃነትና ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ የመሾሙ ጉዳይ ግን ሁለቱን አብያተክርስቲያን ሊያቀራርባቸው አልቻለም። አጣብቂኝ ውስጥ የተገባበትን ጉዳይ ለመፍታት ለማጤንና መልስ ለመስጠት እስክንድርያ ባለመፈለጓ ክርክሩ ረጅም ጊዜ ወሰደ። የቅብጡ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ አዲስ አበባ የመጡ ቢሆንም ያለምንም ሥራ ተቀምጠው ነበር።[28]

በኅዳር ወር ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ሁለተኛ መንፈሳዊ ጉባኤ በአዲስ አበባ ተካሄደ። የስብሰባው መወያያ ጉዳይ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመቀባትና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ራሷን እንድትችል ለማድረግ ባለመፍቀዷ ላይ ነበር። መንፈሳዊ ጉባኤው በጠላት አገዛዝ ስር ነጻ በነበረችው ቤተክርስቲያን ላይ ተመርኩዞ ነጻነት ለማወጅ የተነቃቃ ነበር። በዚህ ጉባኤ እንዲቀመጡ ከተጠሩት ሰባ ሁለት የቤተ ክህነት ሊቃውንት በተጨማሪ ቁጥራቸው በዛ ያለ የጉባኤውን ሐሳብ ለማኀልበት የመጡ ካህናት ነበሩ። ስብሰባውን እንዲካፈሉ የተመደቡ የመንግሥት ባለሥልጣናትም ነበሩ። መንግሥት ረጋ ያለ አቋም ወስዶ በድርድር ነጻነት ለማግኘት ቢያስብም ካህናቱ ግን በጠንካራ ሃይማኖታዊ ብሔርተኝነት መንፈስ የተሞሉና ከነጻነት መልስ ሌላ የሚያረካ ቁም ነገር ይገኛል ብለው የማያስቡ ነበሩ። መንግሥት ያለ እስክንድርያ ቤተክርስቲያን ስምምነት ነጻነትን ማወጅ ቤተክርስቲያኗን ጀማሪ ከማድረጉም በላይ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ውዝግብ ያስከትላል የሚል አቋም ይዞ ነበር። በመጨረሻም የሃይማኖት ብሔርተኞችን የኅላ የነጻነት መንፈስ ወደ ጎን በመተው መንግሥት መልዕክተኞችን ወደ ግብጽ ልኮ ለመደራደር ወሰነ።[29]

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በተለያዩ ጊዜያት ወደ ካይሮ ቢጓዙም የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ባሳየችው አስቸጋሪ የድርድር አቋም ምክንያት ጉዳዩ ሳይቋጭ ዘገየ። የቅብጥ ቤተክርስቲያን አቋሟን በተደጋጋሚ ብትቀይርም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን ቁርጠኛ አቋም ማስለወጥ አልቻለችም። ኢትዮጵያም አቋሟን አጠናክራ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾምና መንፈሳዊ ነጻነቷን እንድትጎናጸፍ መጠየቋን ገፋችበት። እስክንድርያ መንፈሳዊ ልጇን ላለማጣት ወደፊት የሚሾመው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለእስክንድርያው ፓትርያርክ የበታችነቱን የሚገልጽና ያለእርሳቸው ፈቃድ ሌሎች ጳጳሳትን እንዳይሾም ይፈርም በማለት የክርክሩን ሂደት ይበልጥ አጓተቱት። ወደፊት እንደምንመለከተውም ኢትዮጵያዊ ጳጳሳት በተሾሙ ቁጥር ዝርዝር ዘገባው ለእስክንድርያው ፓትርያርክ ይላክላቸው ነበር። በዚህ የክርክር ወቅት የአንደኛው አገር ጋዜጦች የሌላኛውን አገር አቋም በመቃወም ይተቹ ነበር። ይህ ድርጊት ሁለቱን ተደራዳሪ አብያተክርስቲያን ከማቀራረብ ይልቅ ድርድሩን ይበልጥ አጓተተው። የእስክንድርያን ቤተክርስቲያን የአስተዳደር ሥራ እንዲደግፉ የተቋቋሙ መጅሊስ አል-መሊ *(Maglis al-Milli)* የተባሉ ዓለማዊ ሰዎች የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የነጻነት መንፈስ በመቃወም በድርድሩ ሂደት ላይ መቀራረብ እንዳይፈጠር አስቸጋሪ ሁኔታ እየፈጠሩ ነበር። የግብጽ የሙስሊም መንግሥትም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ መንግሥትን የሚቃወሙ ድርጅቶችን ይደግፍ፣ ይረዳና፣ ያስታጥቅ ስለነበር በሃይማኖታዊ ድርድሩ ላይ የበኩሉን ጥላ ጣለበት።[30]

---

[28] *የቤተክርስቲያን መጀመሪያ ቁጥር* (አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣፲፱፻፴ ፰)፣ ገጽ ፲፮-፳፯፤ *የቤተክርስቲያን እድገትና ነፃነት* (አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣፲፱፻፶፬ )፣ገጽ ፳፪-፳፭።

[29] *ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ* (አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፶፪)፣ ፴፪-፴፯፤*Ethiopian Herald*, November 26, 1945, December 3, 1945; *እድገትና ነፃነት*, pp. 77-78.

[30] Wudu, pp. 136-152.

ከብዙ አድካሚና ውጣ ውረድ የበዛበት ድርድር በኋላ የቅብጥ ሲኖዶስ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመቀባት ተስማማ። ይህ ቃል ተፈጻሚ የሚሆነውም የቅብጥ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ካረፉ በኋላ ነበር። አቡነ ቄርሎስ በጣልያን ወረራ ወቅት አገሪቱን ለቀው የሄዱና ከነጻነት መመለስ በኋላም ወደ አገሪቱ መጥተው ካህናቱ ስላገለሏቸው ወደ ካይሮ ተመልሰው ይኖሩ ነበር። በኢትዮጵያ የጳጳሳት ምርጫ የተመረጡት ጳጳሳት ንጉሠ ነገሥቱንና ወራሾቻቸውን በታማኝነት እንደሚያገለግሉ ቃለ መሐላ በመፈጸም ምርጫው በንጉሡ ፀደቀ። የኢትዮጵያ-ቅብጥ ፕሮቶኮል በመጨረሻ በሐምሌ ፲፱፻፵ ዓ.ም ተፈረመ። ጳጳሳት እንዲሆኑ የተመረጡት አምስቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የቅብጥ ፓትርያርክ በታማኝነት ለማገልገል ቃለ መሐላ ፈጽመው ፈረሙ። ከዚያ በኋላ የቅብጥ ፓትርያርክ አቡነ ዮሳብ በሐምሌ ፲፯/፲፱፻፵ ዓ.ም. ካይሮ ከተማ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳቱን ቀብተው ሾሙ። እነርሱም አቡነ ባስልዮስ፣ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቡነ ሚካኤል፣ አቡነ ያዕቆብና አቡነ ጢሞቴዎስ ነበሩ። አቡነ ባስልዮስ በፊት እጨጌ ስለነበሩ የእጨጌውን ማዕረግ ደርበው ያዙት። አዲሶቹ ጳጳሳት አዲስ አበባ በገቡ ጊዜ ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው።[31]

የቅብጡ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በጥቅምት ፲፱፻፵፫ ዓ.ም አረፉ። የእርሳቸው ዕረፍት ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመቀባት የሚያስችለውን መንገድ ጠረገ ። በጥር ወር ፲፱፻፵፫ ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለመምረጥ ጉባኤ ተደረገ። አቡነ ባስልዮስ ድምጽ ብልጫ በማግኘት ተመረጡ። ለመምረጥ ከታደሉት በቁጥር እጅግ ብልጫ የነበራቸው የመንግሥት ሠራተኞች ነበሩ። በጥር ወር ፲፱፻፵፫ ዓ.ም. አቡነ ባስልዮስ ወደ ካይሮ ተጉዘው በአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው የመጀመሪያው ሕጋዊ ሊቀ ጳጳስ ተብለው ተሾሙ። ይህም ማለት በጠላት ወረራ ጊዜ የተሾሙትን ሁለት ሊቃነ ጳጳሳት ግምት ውስጥ ባለማስገባት ነው። ምክንያቱም ከጠላት ወረራ በኋላ የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት እውቅና አልሰጣቸውምና። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ባስልዮስ አዲስ አበባ ሲገቡ ወደ ቤተመንግሥቱ ሄደው ለንጉሠ ነገሥቱ እጅ ነሱ። ለክብራቸውም ፳፩ ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። በመናገሻ ከተማዋ የሚገኙ አብያተክርስቲያን ለብዙ ደቂቃዎች የደወል ድምጽ አሰሙ።[32]

## ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ መሾም

ከጣልያን ጦርነት በኋላ ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር በተደረገው ድርድር የቅብጥ ፓትርያርክ የአቡነ ዮሳብ ድርሻ ቁልፍ ሚና ነበረው። አቡነ ዮሳብ በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም ገና ጳጳስ እያሉ ከቅብጥ ፓትርያርክ ጋር አዲስ አበባ አብረው መጥተው ነበር። በኋላም ራስ ተፈሪ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ሲነግሡ በንግሡ በዓል ላይ ተገኝተው ነበር። የኢትዮጵያ ፍቅርም ነበራቸው። ከሁሉም በላይ አምስት ጳጳሳትን በ፲፱፻፵ ዓ.ም ቀቡ። እንደገናም በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም አቡነ ባስልዮስን ሊቀ ጳጳስ አድርገው ሾሙ። ይህንን በማድረጋቸውና የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንን የራስ አስተዳደር መቻል መብት ሰጥተዋል ተብለው በቅብጥ ጳጳሳትና በመጅሊስ መሊ አባላት ጥርስ ውስጥ ገቡ።

በእነዚህ ምክንያቶች ድርጊታቸውን የተቃወሙ ጥቂት የቅብጥ ጳጳሳት አቡነ ዮሳብን ከመንበረ ፕትርክናቸው በመስከረም ፲፱፻፵፰ ዓ.ም አስወገዷቸው። ከሥልጣን ሲወገዱም በግብጽ ፕሬዚደንት በገማል አብድልናስር መንግሥት ዕውቅናና ድጋፍ ነበር። የኢትዮጵያ ሲኖዶስ አስቸኳይ ስብሰባ አድርጎ የሃይማኖት አባታቸው ያለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዕውቅና መወገዳቸውን በጥብቅ አወገዘ። ችግሩን ለመፍታት እንዲቻል በተለያዩ ጊዜያት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ወደ ካይሮ ተላኩ።

---

[31] *ዜና ቤተክርስቲያን ቁ. ፮፣ ሚያዝያ ፴፣ ፲፱፻፴፰፤ አዲስ ዘመን፣ ግንቦት ፫፣ ፲፱፻፴፰፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ ቁ. ፩፻፬፣ ጥር ፲፰፣ ፲፱፻፵፤ ሰንደቅ ዓላማችን፣ ሐምሌ ፳፩፣ ፲፱፻፵ እና ሐምሌ ፳፰ ፲፱፻፵።*

[32] *አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት ፲፰፣፲፱፻፵፫ እና ጥር ፲፩፣ ፲፱፻፵፫፤ሰንደቅ ዓላማችን፣ ጥር ፪ እና ጥር ፬፣ ፲፱፻፵፫።*

ነገር ግን ፓትርያርኩን ያስወገዱት በቁጥር አነስተኛ የሆኑት ጳጳሳት በጠረጴዛ ዙርያ ቁጭ ብለው ለመደራደር አልፈቀዱም፤ መፍትሔ እንዳይገኝም ማደናቀፉን ቀጠሉበት። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ቡድን በትዕግስት ለአምስት ወራት ያህል ካይሮ ቢቀመጥም ለድርድር ሳይቀራረቡ ቀሩ። ተስፋ በመቁረጥም መልዕክተኞቹ ወደአገራቸው ተመለሱ።[33]

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ ጉዳዩን ገምግሞ ከቅብጥ ቤተክርስቲያን እራሱን ለማግለል ወሰነ። ይህንን ለንጉሠ ነገሥቱ ባሳወቀ ጊዜ በንጉሡ ዘንድ ቀባይነት አላገኘም። ምክንያቱም ንጉሡ በአናሳ የቅብጥ አማኞች ላይ የግብጽ እስላማዊ መንግሥት የሚያደርገውን ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ በመገንዘብና ወደፊት ሊደርስባቸው የሚችለውን ጥቃት በማሰብ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ራሳቸውን የግብጽ ኮፕቶች ተከላካይ አድርገው ሲቆጥሩ የግብጹ ንጉሥ ናስርም ራሱን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ተከላካይ ያደርግ ነበር።[34]

እንደገና የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ወደ ግብጽ ተጉዘው ሌላ ድርድር እንዲካሄድ ጠየቁ። ከሥልጣን በተወገዱት ፓትርያርክ ጥያቄ የቅብጥ ሲኖዶስ ተሰበሰበ። በዚህ ሲኖዶስ የኢትዮጵያን ሲኖዶስ የወከሉ ጳጳሳት ተሳታፊ ነበሩ። አቡነ ዮሳብን ካስወገዱት ጳጳሳት በቁጥር የሚበዙት የሲኖዶሱ ተሳታፊ ሆኑ። ፓትርያርኩን ወደ ሥልጣን ለመመለስ ስምምነት ላይ ደረሱ። ይሁንና ፓትርያርኩን ወደ ካይሮ ለመመለስ በታቀደበት ዕለት ከኢትዮጵያውያኑ ጳጳሳት በስተቀር የተገኘ አልነበረም። ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በውሳኔው መሠረት በድፍረት ፓትርያርኩን ይዘው በባቡር ወደ ካይሮ ተጓዙ። ዕለቱ የግብጽ ፕሬዚደንት ሆነው የተመረጡት ናስር የምረቃ በዓል የሚካሄድበት ነበር። ኢትዮጵያውያኑ ከፓትርያርኩ ጋር ካይሮ በፓትርያርኩ መኖርያ ሲደርሱ የገጠማቸው በደስታ የሚቀበላቸው ሳይሆን ተቃዋሚዎች ብቻ ነበሩ። የፓትርያርኩ መኖርያ በተቃዋሚዎችና በወታደሮች ታጥሮ አገኙት። ተቃዋሚዎች ፓትርያርኩን ነጥቀው በመውሰድ ታመዋል በማለት ሆስፒታል ውስጥ አስገቧቸው። ኢትዮጵውያኑ ጳጳሳት በተፈጠረው አሳዛኝ ገጠመኝ አዝነው ወደ አገራቸው ተመለሱ።[35]

መልዕክተኞቹ ካይሮ ያጋጠማቸውን ሁኔታ ለንጉሡ በማስረዳት ከእንግዲህ ወዲህ ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር አብረው ለመሥራት እንደሚቸግራቸው ገለጹ። አቡነ ዮሳብ ወደ መንበራቸው ሳይመለሱ ሆስፒታል ውስጥ በኅዳር ወር ፲፱፻፵፱ ዓ.ም ዐረፉ። ዕረፍታቸውም በሁለቱ አብያተክርስቲያን መካከል ያለውን ሁኔታ አባባሰው። ወዲያውኑም የግብጹ እስላማዊ መንግሥት አዲስ የምርጫ ሕግ አጸደቀ። ይህም ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር ቀደም ብሎ የተደረሰበትን ውል በመሻር ነበር። ከዚህ የተነሳ የኢትዮጵያ ሲኖዶስ ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር ለመሥራት አልፈቀደም። ካይሮ ላይ የተመረጡትን ዐቃቤ መንበር ላለማወቅ ወሰነ። ለፓትርያርክ ምርጫ ኢትዮጵያ እንድትገኝ ብትጋበዝም ፈቃደኛ አልሆነችም።[36]

ከዚህ ባሻገር የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የቅብጥ ቤተክርስቲያን መልስ ልትሰጥባቸው የማትችለውን ጥያቄ አቀረበች። ዋናው ጥያቄ በቅብጥ ፓትርያርክ ምርጫ ውስጥ ስለሚኖራት ድርሻ ነበር። ሌሎች ጥያቄዎች ኢትዮጵያ በቅብጥ ፓትርያርክ አስመራጭ ኮሚቴ ውስጥ በብዛት እንድትወክልና በመራጭነት ትልቅ የቁጥር ድርሻ እንዲኖራት ነበር።

[33] *ዜና ቤተክርስቲያን*፣ ቁ. ፲፩፣ መስከረም ፴፣ ፲፱፻፵፰ ፤*Ethiopian Herald*, December 3, 1955 and January 5, 1956.

[34] Wudu, pp. 171-187.

[35] *Ibid.*, pp. 167-202

[36] *Ibid*.

ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያዊያን ለፓትርያርክነት ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ነበር። ይህ ማለትም ኢትዮጵያ ከዚህ ዘመን በፊት ያልነበራትን መብት ለማግኘት የሚያስችላት ነበር። የኢትዮጵያ ጥያቄ የቅብጥ ሲኖዶስን በእጅጉ አስደነገጠ። ኢትዮጵያውያን ለፓትርያርክነት ከተወዳዳሩ፣ በምርጫ ኮሚቴና በመራጭነት በብዛት ከተሳተፉ የቅብጥን የሥልጣን ቁልፍ የሚፈታተን ነበር። ምናልባትም የቅዱስ ማርቆስን መንበር ወደ አዲስ አበባ ሊያዛውር በቻለ ነበር።[37] ቅብጦች በዚህ ጉዳይ በምንም ዓይነት ሁኔታ ለመደራደር አይችሉም ነበር። ሊያደርጉ ቢያስቡም የእስላማዊ መንግሥቱ በአገር ክህደት ሊጠይቃቸው ይችል ነበር።

የመደራደሪያ ቀዳዳ ባለመገኘቱ ሁለቱ አብያተክርስቲያን ከገቡበት አጣብቂኝ ለመውጣት አልተቻላቸውም። አዲስ የወጣው የቅብጥ ቤተክርስቲያን ሕግ ኢትዮጵያ ዕውቅና ሳትሰጠው ፀደቀና ታተመ። አዲሱ የቅብጥ ፓትርያርክ ያለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሳትፎ ተመረጡ። ኢትዮጵያ ሳትሳተፍም በዓለ ሲመታቸው ተከበረ። ሁለቱ አብያተክርስቲያን በመለያየት አፋፍ ላይ እያሉ ነበር አዲሱ የቅብጥ ፓትርያርክ ችግሩን ለማርገብ ለማቀራረብ የሚያስችል ርምጃ የወሰዱት። ይህም ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሱን ወደ ፓትርያርክ ማዕረግ ለማሳደግ ነበር። ሐሳባቸው ኢትዮጵያን የሚጠቅም በመሆኑ ኢትዮጵያም በደስታ ተቀበለችው።[38]

የተደረሰበትን መግባባት ለመቋጨት ሲባል በሁለቱ አብያተክርስቲያን መካከል ካይሮ ላይ በሐምሌ ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ስምምነት ተፈረመ። በስምምነቱ መሠረት የግብጹ ፓትርያርክና ፖፕ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ከፍተኛ አባት እንዲባሉ ተስማሙ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መሪም ፓትርያርክና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የሚል ማዕረግ እንዲይዙ ሆነ። አዲሱ የ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ውል ከዚህ በፊት የተደረጉትን ውሎች የሚተካ ነበር። ከዚህ ሁሉ በኋላ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነው እንዲቀቡ ንጉሠ ነገሥቱ ለቅብጡ ፓትርያርክና ፖፕ ደብዳቤ ጻፉ። በበዓለ ሢመቱ ላይ ለመገኘትም ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተሰቦቻቸውና ከሚኒስትሮች ጋር ወደ ካይሮ ተጓዙ። እግረ መንገዳቸውንም ለጉብኝት ወደ ሞስኮ ይጓዙ ነበር። የአቡነ ባስልዮስ በዓለ ሢመት ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ካይሮ ላይ ተካሄደ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያው ፓትርያርክ ሆኑ። ከብዙ ዓመታት እልህ አስጨራሽ ድርድር በኋላ ቤክርስቲያኗ የራሷን መሪ አገኘች። በአዲስ አበባ የሚታተመው የእንግሊዘኛ ጋዜጣ *የኢትዮጵያ ሔራልድ* በጥሩ ሁኔታ እንደገለጸው ድርጊቱ ሁለቱን አገራት ይበልጥ ያቀራረበ ነበር።[39] የፓትርያርኩ ሹመት ለብዙ ዘመናት የተካሄደውን የሃይማኖታዊ ብሔረተኝነት እንቅስቃሴ ያጠቃለለ ትልቅ ድል ነበር። ብዙዎች የታገሉለትና የጮሁለት ጥያቄ የተመለሰበት ነበር።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጥገኝነት እንድትላቀቅ ለማድረግና አገራዊ ጳጳሳትን ለማፍራት ለብዙ ዘመናት አድካሚ ትግል ተካሂዷል ። ለዚህም ሃይማታኖታዊ ብሔርተኞች ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል ። ከብዙ ዘመናት ውጣ ውረድና እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ በ፲፱፻፳፪ ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ተቀቡ። ምንም እንኳ በጠላት ዘመን የተፈጸመ ቢሆንም በጣልያን ጊዜ ሁለት ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት ተሹመዋል።

[37] *Ibid*

[38] *Ethiopian Herald*, June 9, 1959, June 29, 1959; *አዲስ ዘመን፣* ግንቦት ፳፰፣ ፲፱፻፶፩ እና ሰኔ ፳፫፣፲፱፻፶፩።

[39] *Ethiopian Herald*, July 29, 1959.

ይህንን ታሪካዊ ድርጊት ተመርኩዞ ከጠላት ወረራ በኋላ የበለጠ ነጻነት ለማግኘት ትግሉ ቀጠለ፡፡ መንፈሳዊ ድርድሩን ዓለማዊና ፖለቲካዊ ጥላ ቢጥልበትም በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ሕጋዊ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ተሾመ፡፡ ቀጥሎም በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም የመጀመሪያው ፓትርያርክ ለመሾም በቃ፡፡

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት አቡነ ባስልዩስ ነበሩ፡፡ እርሳቸው ከ፲፱፻፶፩ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፷፪ ዓ.ም. ድረስ በዚሁ ሓላፊነት ሰርተዋል፡፡ ቀደም ብሎም የቤተክርስቲያኗ እጨጌና የሸዋ ሊቀ ጳጳስ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ከቅብጥ ቤተክርስቲያን ጋር የተደረገውን የነጻነት ድርድር በሓላፊነት በመምራት የአገራቸው ቤተክርስቲያን ራሷን እንድትችል አድርገዋል፡፡ መርሳት የማይኖርብን ነገር ቢኖር ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ የቤተክርስቲያኗን ነጻነት ለማስገኘት ያደረጉትን ጥረትና ያሳዩትን መንፈሳዊና ፖለቲካዊ አመራር ጥልቀት ነው፡፡

አቡነ ባስልዮስ በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በአገሪቱ በፈነዳው የአብዮት ማዕበል ወቅት ከመንበራቸው ከተወገዱ በኋላ በእስር ላይ እንዳሉ ተገድለዋል፡፡ በደርግ የሥልጣን ዘመንም አቡነተክለሃይማኖትና አቡነመርቆርዮስ በተከታታይ ተመርጠው ቤተክርስቲያናቸውን አገልግለዋል፡፡ ከደርግ ዘመን ውድቀት በኋላ ሁለተኛው የደርግ ፓትርያርክ ከሥልጣን ወርደው አቡነ ጳውሎስ ተመርጠው ቤተክርስቲያኗን በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ፡፡

ለዘመናት የተካሄደው የሃይማኖት ብሔርተኝነት ትግል ካስገኘው ድል ትልቁና ዋናው ቤተክርስቲያኗ በራሷ ሕግ መመራት መቻልዋና የራሷ የሆነ አመራር እንዲኖራት ማድረጉ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ ፻፳፬ የሚሆኑ ሊቃነ ጳጳሳት ተሹመዋል፡፡ ብዛት ያላቸው አህጉረ ስብከት ተከፍተዋል፡፡ የዲቁናና የቅስና ሹመት ለማግኙት አዲስ አበባ ድረስ ይደረግ የነበረው አድካሚ ጉዞ ቀርቶ በየክፍለ ሀገራቸው መዲና ሹመት ማግኘት ችለዋል፡፡ በሀገራዊ ሊቃነ ጳጳሳት ስብከተ ወንጌል ተስፋፍቷል፡፡ ብዛት ያላቸው መንፈሳዊ መጽሐፍት ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል፤ወደ ሌሎችም ቋንቋዎች የመተርጎሙ ሥራ ተጀምሯል፡፡

የመጀመርያው ፓትርያርክ ከተሾመበት ከ፲፱፻፶፩ ዓ.ም ጀምሮ አያሌና ዐበይት የሥራ ክንውኖች ተፈጽመዋል፡፡ ያልተፈጸሙም አሉ፡፡ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ተከስተው ነበር፡፡ ቤተክርስቲያኗ ልትፈጽማቸው የሚገቧት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋነኛው የገጠር አብያተክርስቲያንን መደገፍና ማጠናከር ነው፡፡ በገንዘብ አቅም ሲጐለብቱ አሁን የሚታየው የካህናት ፍልሰት የሚገታበት ነገር በጊዜ ብዛት ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር ጎን ለጎን ጥንታዊ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን ማጠናከር ተተኪ አገልጋዮችን ለማፍራት ያስችላል፡፡ የአስተዳደር መሻሻልና፣ ዘመናዊ የገንዘብና የንብረት አያያዝ ዘዴ ሲታከልበት ውጤቱ አመርቂ ይሆናል፡፡ በተለይም ከመንፈሳዊ ኮሌጆች የሚመረቁ ካህናት በቂ ሥልጠና አግኝተው በገጠር በመሰማራት የቤተክርስቲያኗን ሥራ እንዲያጠናክሩ ለማድረግ በቂ ክትትልና አመራር መስጠት ይገባል፡፡